በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ

መመሪያ ቁጥር 147/2016

በመንግስት ትምህርት ቤት መዋቅር ክለሳ ጥናት መሰረት ለተዘጋጁ የሥራ መደቦች የዋና ርዕሰ መምህራንና ምክትል ርዕሰ መምህራን የድልድል አፈፃፀም መመሪያ

መስከረም/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለከተማው ነዋሪ የሚሰጠውን የአጠቃላይ ትምህርት አገልግሎት ግልጽ፣ ፈጣንና ውጤታማ እንዲሆንና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ በርካታ የለውጥ ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ከነዚህ ለውጦች መካከል ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የአጠቃላይ ትምህርት አደረጃጀቶችን እንደገና በማደራጀት ወደ ስራ መግባቱ ዋና ማሳያ ነው፡፡ በዚህም በቢሮ በ 9 አላማ ፈፃሚ ዳይሬክቶሬቶች፣ በክ/ከተማ በ 6 ቡድኖችና የሱፐርቪዥን ክላስተር ቡድኖች፣ በወረዳ በ 2 ቡድኖችና የሱፐርቪዥን ክላስተር ቡድኖች ተደራጅቶና የሰራተኞች ድልድል በመመሪያው መሰረት ተካሂዶ በአዲስ አደረጃጀትና በተለወጠ ሰራተኛ ስራ በመጀመሩ፤

ይህ የለውጥ አሰራር ዳር እንዲደርስና ውጤታማ እንዲሆን የትምህርት ሴክተሩ ዋና አካል የሆነው ትምህርት ቤት በመዋቅራዊ አደረጃጀቱ እንደገና ሊቃኝና ዋና ር/መምህራንና ም/ር/መምህራን በአዲስ መንገድ ሊደለደል ስለሚገባ አዲስ የትምህርት ቤቶች መዋቅር አደረጃጀት በመዘጋጀቱ፤

በዚህ መዋቅራዊ አደረጃጀት ጥናት ለተዘጋጁት ሁለቱ የስራ መደቦች ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ጋር የሚጣጣም የአፈፃፀም መርህና ቅደም ተከተልን መሠረት ያደረገ በጥናቱ ለሥራ መደቦቹ በተሰጠው ደረጃ ለማወዳደር እና ለመደልደል የሚያስችል አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም ጸድቆ በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን በትምህርት ቤት መዋቅር ክለሳ ጥናት ለተዘጋጁ የሥራ መደቦች የዋና ር/መምህራንና ም/ር/መምህራን የድልድል አፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>፤

   ይህ መመሪያ *" በመንግስት ትምህርት ቤት መዋቅር ክለሳ ጥናት መሰረት ለተዘጋጁ የሥራ መደቦች የዋና ርዕሰ መምህራንና ምክትል ርዕሰ መምህራን የድልድል አፈፃፀም መመሪያ* ***ቁጥር*** *147/ 2016"* ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

2. <u>**ትርጓሜ**</u>፤

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤-

   1. **«አዋጅ»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 ነው፤
   2. **«ከተማ»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ማለት ነው፤
   3. **«ቢሮ»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ነው፤
   4. **«ትምህርት ቢሮ»** ማለት በመማር ማስተማር ዙሪያ ሃላፊነትን ወስዶ የሚሰራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ማለት ነው፤
   5. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽህፈት ቤትን ማለት ነው፤
   6. **"ትምህርት ጽ/ቤት"** ማለት የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤትን ማለት ነው፤
   7. **«የመንግሥት ሠራተኛ»** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር ባሉ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ ነው፤
   8. **«ውድድር»** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ጸድቆ በወረደው መመሪያ መሰረት በክፍለ ከተማ ለ2ኛ ደረጃ፤ በወረዳ ለቅድመ 1ኛ እና መካከለኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዋና እና የምክትል ር/መምህራንን ስራ መደቦች ላይ የሚያመለክቱትን ለማወዳደር ነው፤
   9. **«ድልድል»** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ጸድቆ በወረደው የድልድል መመሪያ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ

አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በጸደቀው የትምህርት ቤቶች መዋቅር ጥናት ለተዘጋጁ የዋና ር/መምህራንና ም/ር/መምህራን የስራ መደቦች በአፈፃፀማቸው፣ በሥነ-ምግባራቸው እና የተፈላጊ ችሎታ መስፈርትን አሟልተው በውድድር ኮሚቴው የተመረጡ ተወዳዳሪዎችን በትምህርት ቤቶች መደልደል ነው፤

10. **«ትምህርት ቤት»** በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ፣ አጠቃለይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማለት ነው፤

11. **«የትምህርት ቤት ደረጃ»** ማለት በውጪ ኢንስፔክሽን ምዘና የትኩረት መስኮች ከግብዓት፣ ከሂደት እና ውጤት መስተጋብር ልኬት አንፃር የተፈረጀበት ደረጃ ማለት ነው፤

12. **«ምዘና»** ማለት ዋና ርዕሳነ መምህራን፣ ምክትል ርዕሳነ መምህራን በተቀመጠው የደረጃ መለኪያ መስፈርት/ስታንዳርድና የትምህርት ቤቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ በተዘጋጀው ዕቅድ መሰረት አፈፃፀም የሚለካበት ማለት ነው፤

13. **«የበላይ ኃላፊ»** ማለት መስሪያቤቶቹን በበላይነት የሚመሩ ዋና እና ምክትሎቹ ናቸው ማለትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሃላፊና ምክትሎች፣ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች፣ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች፣ የትምህርት ቤት ር/መምህራንና ምክትሎች፣ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት ቢሮ ሃላፊዎችና ምክትሎች ማለት ነው፤

14. «ዋና **ርዕሰ መምህር**» ማለት አጠቃላይ ትምህርት ቤቱን በበላይነት የሚመራ ሃላፊ ማለት ነው፤

15. **«ምክትል ርዕሰ መምህር»** ማለት ለዋና ርእሰ መምህሩ ተጠሪ የሆነ ትምህርት ቤቱን በምክትልነት የሚመራ ሃላፊ ማለት ነው፤

16. **«የሥራ መደብ»** ማለት በአንድ የመንግስት ትምህርት ቤት ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

17. **«ሜሪት»** ማለት በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በችሎታና በብቃት ላይ ተመሥርቶ አመልካቾች በሚያሟሉበት ቦታ በማወዳደር ድልድል መፈጸም ነው፤

18. **«ተፈላጊ ችሎታ»** ማለት የውድድሩ ዝቅተኛ የትምህርት እና የስራ ልምድ መስፈርት ማለት ነው፤

19. «**ደመወዝ**» ማለት በአንድ የሥራ ደረጃ ለተመደቡ ሥራዎች የተወሰነ መነሻ ክፍያ ነው፤
20. "**የአካል ጉዳተኛ**" ማለት በደረሰበት የአካል፣ የአእምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ተከትሎ የሚመጣ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊ ወይም የባህላዊ መድሎ ሳቢያ በስራ ስምሪት የእኩል እድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው፤
21. «**ተዛማጅ ወይም አግባብነት የትምህርት ዝግጅት**» ማለት በመዋቅር ክለሳ ጥናት ከተዘረዘሩት የትምህርት አይነቶች ጋር የስራ መደቡን ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችለውን ኮርስ የወሰደ ስለመሆኑ የሚገናዘብበት ነው፤
22. "**አግባብነት ያለው የስራ ልምድ**" ማለት በዚህ መመሪያ ሰራተኞች የሚወዳደሩበት የስራ መደብ ከድልድሉ በፊት ካላቸው የስራ ልምድ ጋር ያለው ግንኙነት ማለት ነው፤
23. «**የድልድል ኮሚቴ**» ማለት በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋም እና በተቀመጡ የሥራ መደቦች ላይ በተዘጋጀው መስፈርት መሠረት ተወዳደሪዎችን አወዳድሮ ድልድል በመስጠት የውሣኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ ነው፤
24. «**ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ**» ማለት በመዋቅር ክለሳ በፀደቁ የሥራ መደቦች ላይ በሚካሄድ ውድድር የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርና የውሣኔ ኃሣብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ ነው፤
25. «**ተወዳዳሪ**» ማለት በዋና ር/መምህር እና በም/ር/መምህር የስራ መደብ ላይ ለውድድር የቀረቡ መምህራን፣ ዋና ር/መምህራን እና ም/ር/መምህራን ማለት ነው፤
26. **የፆታ አገላለጽ፡-** በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3 <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ተፈፃሚነት የሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 56/2010 በሚተዳደሩ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ሆኖ በመዋቅር የክለሳ ጥናት ለፀደቁ የዋና ር/መምህራንና ም/ር/መምህራን የሥራ መደቦች ከመምህራን፣ ዋና ር/መምህራን እና ም/ር/መምህራን መካከል አወዳድሮ ምደባ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ አንድ ክፍለ ከተማ የራሱን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በክፍለ ከተማው ስር ባሉ ወረዳዎች ስር የሚገኙ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ድልድል ለመስራት ይሆናል፡፡

4 የመመሪያው ዓላማ

የትምህርት ቤቶችን አመራር፣ አስተዳደርና አሰራር በማስተካከል ውጤታማ የመማር ማስተማር ስርአት ለማስፈን እንዲቻል የዋና ር/መምህርነትና ም/ር/መምህርነት ስራ መደብን በግልጸኝነት፣ በፍትሃዊነትና በተጠያቂነት አወዳድሮ በመደልደል ትምህርት ቤቶችን ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

5. የመመሪያው መርህ

የዋና ርእሰ መምህራንና ም/ር/መምህራን መደብ ውድድርና ድልድል የሚከተሉትን መርሆች ባሟላ መልኩ ይከናወናል፤-

1. ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል፤
2. የሜሪት ሥርዓትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፤
3. ብቃትንና ተፈላጊ ችሎታን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን ሠራተኛ በትክክለኛው ቦታ የሚለውን መርህ የተከተለ ይሆናል፤
4. ተፈላጊ ችሎታ ለሚያሟሉ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተወዳዳሪዎችን በሚያበረታታ መልኩ መከናወን አለበት፤
5. የዋና ርእሰ መምህራን፣ ም/ር/መምህራን ድልድል ውጤት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በሚስጥር መያዝ አለበት፤
6. በስነ-ምግባሩ፣ በብቃቱና በአገልጋይነቱ የዳበረ መምህር፣ ዋና ር/መምህርና ም/ር/መምህር በአግባቡ በመለየት ተግባራዊ ይሆናል፤

ክፍል ሁለት

ስለዋና ርዕሰ መምህራን እና ምክትል ርዕሰ መምህራን ውድድር አፈፃፀም

6. የውድድር አፈጻጸም

የውድድሩ አፈጻጸም የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች መሠረት ያደረገ ይሆናል፤-

1. የቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በወረዳ ደረጃ በሚዋቀር የድልድል ኮሚቴ እና በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ አማካይነት የሚከናወን ይሆናል፤
2. የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በክፍለ ከተማ ደረጃ በሚዋቀር የድልድል ኮሚቴ እና በክፍለ ከተማው የትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ አማካይነት የሚከናወን ይሆናል፤

3. በዚህ መመሪያ ድልድል የሚካሄደው በትምህርት ቤቶች መዋቅር ጥናት መሰረት ደረጃ በወጣላቸው የዋና ርዕሰ-መምህራን እና ምክትል ርዕሰ-መምህራን መደቦች ላይ ብቻ ይሆናል፤

4. ማንኛውም ተወዳዳሪ ሲቀርብ የሚጠየቀውን የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ የግድ ማሟላት የሚጠበቅበት ይሆናል፤

5. ለዚህ ድልድል ማንኛውም ተወዳዳሪ **እስከ ሁለት** የሥራ መደቦች ተመዝግቦ መወዳደር ይችላል፤

6. ማንኛውም ተወዳዳሪ ተፈላጊ ችሎታውን ቅድሚያ ሳያሟላ በአጠቃላይ ከ100% የነጥብ ውጤቱ ከፍተኛ ነጥብ በማግኘቱ ብቻ ለውድድር መቅረብ አይችልም፤

7. በውድድሩ ምክንያት ተበልጠው ስራ መደብ ያላገኙ ተወዳዳሪዎች፤-

   ሀ) መምህራን የነበሩት በመምህርነት ስራቸው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፤

   ለ) ዋና ርዕሰ-መምህራንና ምክትል ርዕሰ-መምህር የነበሩ በመጀመሪያ ወይም 2ኛ ዲግሪ በተመረቁበት የትምህርት አይነት ወደ መምህርነት የሚመደቡ ይሆናል፤

   ሐ) የትምህርት ዝግጅታቸው በክፍል ውስጥ ከሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ጋር የማይገናኝ ከሆነ ወደ ፐብሊክ ሰርቪስ የባለሙያ የስራ መደቦች ላይ እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡

8. በትምህርት ቤቱ፣ በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት፣ በክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት እና በትምህርት ቢሮ እቅድ መሠረት ተፈቅዶለት አንድ ዓመት እና በላይ በሚፈጅ ትምህርት ወይም ሥልጠና ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በዚህ ምደባ ውድድር ውስጥ አይካተትም፤

9. በቅርቡ ከአመራርነት ተነስተው በዋና ር/መምህርነትና ም/ር/መምህርነት የተመደቡ አመራሮች፡-

   ሀ) ምደባው ከሶስት ወር በፊት ከሆነ ተመድቦ ካገለገለበት ጊዜ ጀምሮ ታሳቢ ተደርጎ የስራ አፈጻጸም እንዲሞላለት ይደረጋል፤

   ለ) ምደባው ከሶስት ወራት ወዲህ ከሆነ ግን አሁን የተመደቡበት የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊና በሹመት ሲሰሩበት ከነበረው ተቋም ጋር በመሆን /መረጃዎችን በማጥራት/ እንዲመዘንና ለውድድር እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

10. ተወዳዳሪዎች በሁለቱም የስራ መደቦች ላይ በሚያመለክቱበት ወቅት የስራ አፈጻጸም ውጤት የተለያየ አድርጎ መሙላት አይቻልም፤

11. የሥራ ልምድም ሆነ የትምህርት ዝግጅት መረጃ የሚያዘው የድልድል ኮሚቴው ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ በወሰነው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፤

12. በሰው ሀብት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ትምህርት ቤቱ ፈቅዶና ዕውቅና በሰጣቸው ምክንያቶች በድልድል ወቅት በሥራ ላይ ያልተገኘ መምህር፣ ዋና ርዕሰ-መምህርና ምክትል ርዕሰ-መምህር በሚከተሉት ሁኔታዎች የሚወዳደር ይሆናል፡-

ሀ) በትምህርት ቤቱ የሰው ሀብት አስተዳደር መረጃ አቅራቢነት ሠራተኛው በህመም ፈቃድ ወይም በወሊድ ፈቃድ ወይም በዓመት ፈቃድ ወይም ያለደመወዝ ፈቃድ ወይም እስከ 3 ወራት አጭር ስልጠና ላይ የሚገኝ መሆኑን በጽሁፍ ማረጋገጫ የሰጠበት ከሆነ የመወዳደሪያ መስፈርቱን አሟልቶ መወዳደር ይችላል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12 (ሀ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ቤቱ የሰው ሀብት አስተዳደር ያቀረበውን መረጃ የድልድል ኮሚቴው ሲያረጋግጥና ሲፈቅድ የሚወዳደር ይሆናል፡፡

13. በተለያየ ምክንያት በእስር ላይ የሚገኝ ተወዳዳሪ በዚህ ውድድር ውስጥ አይሳተፍም፤

14. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (13) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ታስረው የተለቀቁ ተወዳዳሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡-

ሀ) በእስር ላይ የቆዩት ከስድስት ወራት በታች ሆኖ የተለቀቁ ከሆነ የውድድሩ ስራ ከመጀመሩ በፊት ለትምህርት ቤቱ ሪፖርት ያቀረበ መወዳደር ይችላል፤

ለ) በእስር ላይ የቆዩት ከስድስት ወር በላይ ከሆነና በነፃ ከእስር ስለመለቀቁ በቂ የሆነ ማስረጃ ይዘው ከቀረቡ የውድድር ስራው ከመጀመሩ በፊት ማመልከት ከቻሉ ብቻ ለውድድር መቅረብ ይችላሉ፡፡

15. ቀደም ሲል ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ውሳኔ ያለባቸውና የቅጣት ጊዜያቸውን ያልጨረሱ መምህራን፣ ዋና ርዕሰ-መምህራንና ምክትል ርዕሰ-መምህራን በዚህ ውድድር አይሳተፉም፤

16. በዲሲፕሊን ክስ በሂደት ላይ ያሉና ውሣኔ ያላገኙ የዲስፕሊን ጉዳዩች ያለባቸው ተወዳዳሪዎች ሲያጋጥሙ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ሀ) በዚህ ውድድር ወቅት እንደመስፈርት ተይዘው ተወዳዳሪውን ከውድድርና ከድልድል አያግዱትም፤

ለ) ነገር ግን የዲሲፕሊን ሂደቱ ሲያልቅ በከባድ ዲሲሰፕሊን የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ ከተደለደለበት መደብ ይነሳል፡፡

17. ውድድር የሚጀምረው ከከፍተኛው መደብ/ደረጃ ከዋና ርዕሰ-መምህር ስራ መደብ ጀምሮ ወደ ምክትል ርዕሰ-መምህር የሥራ መደብ ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ይሆናል፤

18. በውድድር አፈጻጸም ሂደት አሸናፊ የሚሆነው ተወዳዳሪ ደሞዝና ደረጃ ጉዳይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይወሰናል፡-

ሀ) ከስራ መደቡ መነሻ በታች ደመወዝ የሚከፈለው የመነሻውን የደመወዝ ክፍያ ያገኛል፤

ለ) የስራ መደቡን ደረጃ ደመወዝ ደርሰውበት ወይም አልፈውት ከሆነ ምንም ዓይነት ጭማሪ ሳይደረግ ሲከፈላቸው የነበረውን ይዘው የሚቀጥሉ ይሆናል፤

ሐ) ከስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን የደመወዝ ስኬል ጋር የማይገጥም የደመወዝ መጠን

ሲያጋጥም ወደ ጎን የሚገኘውን የእርከን ደመወዝ ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡

19. አፋን ኦሮሞ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች ከአመራሮቹ ቢያንስ አንዳቸው ቋንቋውን ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ መሆናቸው በፈተና ተረጋግጦ ውድድርና ድልድል ይካሄዳል፤

20. ተወዳዳሪዎች በመምህራን የደረጃ እድገት መሰላል የመምህርነት ደረጃ እና ከዛ በላይ የደረሱ መሆን አለባቸው፤

21. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 20 እንደተጠበቀ ሆኖ በዋና ርዕሰ-መምህርነትና ምክትል ርዕሰ-መምህርነት መደብ ላይ እያገለገሉ ያሉ ነገር ግን ልምዳቸው ከ 5 አመት በታች የሆኑ ተወዳዳሪዎች ካሉ በዚህ ውድድር መሳተፍ ይችላሉ፡፡

7. <u>የትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ፣</u>

የድልድል ኮሚቴው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የትምህርት ዝግጅት መስፈርቶች መከተል አለበት፡-

1. ውድድሩ የሚካሄደው በትምህርት ቤቶች መዋቅር ክለሳ ጥናት መሰረት በተቀመጠው በስነ-ትምህርት ወይም በአፕላይድ የትምህርት ዝግጅት ኖሮአቸው ፒጂዲቲ የወሰዱ ወይም የትምህርት አመራርና አስተዳደር የትምህርት ዝግጅት ጋር የተያያዘ ብቻ ይሆናል፤
2. በማንኛውም ደረጃ ያልተጠናቀቀ የትምህርት ደረጃ ለድልድል ስራው ተግባራዊ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

3. የሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃዎች ከምርቃት በኂላ ቢያንስ ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የተሰጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

8. የሥራ ልምድ በተመለከተ፤

የድልድል ኮሚቴው ተወዳዳሪዎችን ሲያወዳድር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የስራ ልምድ መስፈርቶች መከተል አለበት፡-

1. አንድ ተወዳዳሪ ለሚወዳደርበት የሥራ መደብ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ለድልድል ይያዝለታል፤
2. ተፈላጊ ችሎታው የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ በሚጠይቁ የስራ መደቦች ላይ ለሚደረገው ውድድር፡-

   ሀ) የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ከተጠናቀቀ በኂላ የተገኘ አግባብ ያለው የአንድ ዓመት የሥራ ልምድ እንደ አንድ ዓመት ይያዛል፤

   ለ) የቲቲአይ ወይም ሰርተፍኬት ምሩቃን አገልግሎት አንዱ አመት እንደ ግማሽ ተይዞ የሚቆጠር ይሆናል፡፡
3. በአመራርነት ሲያገለግል የነበረ ሹመኛ ቀደም ሲል በሹመት ሲያገለግልበት የነበረው ስራ ልምዱ በቀጥታ እንዲያዝ ይደረጋል፤
4. ለአንድ የሥራ መደብ ተፈላጊ ችሎታውን የሚያሟሉ ሁለትና ከዚያ በላይ ተወዳዳሪዎች ሲቀርቡ ተወዳዳሪዎችን ለመለየት ለውድድር የሚያዘው የሥራ ልምድ ሠራተኛው ያለው ልምድ ሆኖ ከዓመት፣ እስከ ወርና ቀን ድረስ ተሰልቶ ይሆናል፡፡

ክፍል ሶስት

የምዘና መስፈርት እና ነጥብ አሰጣጥ ሂደት

9. የምዘና መስፈርትና ነጥብ አሰጣጥ ሂደት

1. ይህ የመመዘኛ መስፈርት ተወዳዳሪዎችን በሚመጥናቸው የስራ መደብ ላይ ለማወዳደሪያነት የሚያገለግል ይሆናል፤
2. የሚመለከታቸው አካላትም ይህን በመረዳት የመመዘኛ መስፈርቱን በአግባቡ ወይም በትክክል መሙላት ይጠበቅባቸዋል፤

3. ለ1ኛ ደረጃ ዋና ር/መምህርነትና ም/ር/መምህርነት መደብ የመወዳደሪያው ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ ሲሆን ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ የሆነ ትምህርት ዝግጅትም መወዳደር ይቻላል፤
4. ለ2ኛ ደረጃ ዋና ር/መምህርነትና ም/ር/መምህርነት መደብ የመወዳደሪያው ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ሁለተኛ ዲግሪ ነው፤
5. ለዋና ርእሰ መምህርነትና ለምክትል ርእሰ መምህርነት ለሚወዳደሩ ተወዳዳሪዎች ከታች በሰንጠረዥ1 የተቀመጠውን ከተራ ቁጥር 1-6 ከ100% ያገኙት ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

10.የድልድል መመዘኛ መስፈርትና የነጥብ አሰጣጥ ክብደት

ሰንጠረዥ1፡- የድልድል መመዘኛ መስፈርትና የነጥብ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል

ተ.ቁ	የመመዘኛ መስፈርቶች	የማወዳደሪያ ነጥብ (ከ100%)
1	ለትምህርት ዝግጅት የሚሰጥ ነጥብ፣	10
2	ለስራ ልምድ አገልግሎት የሚሰጥ ነጥብ፣	5
3	ለውጤት ተኮር የስራ አፈፃፀም ምዘና፣	30
4	የማህደር ጥራት፣	5
5	ለፈተና ውጤት (የጽሁፍ 15፣ የቃል 5) (ለአፋን ኦሮሞ ተናጋሪዎች ፈተናው በአፋን ኦሮሞ ተዘጋጅቶ ይሰጣል)፡፡	20
6	ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ብቃት በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ የሚሰጥ የሚሠጥ ነጥብ፣	30
	ድምር	**100**

11.ለትምህርት ዝግጅት የሚሠጥ ነጥብ አፈፃፀም

ማንኛውም ተወዳዳሪ ለስራ መደቡ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት አሟልቶ ለውድድሩ ከተመዘገበ በኂላ ለትምህርት ዝግጅት የሚሰጠው ነጥብ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ2፡- ለትምህርት ዝግጅት የሚሠጥ ነጥብ እንደሚከተለው ይሆናል

ተ.ቁ	የማወዳደሪያ መስፈርት	የሚሰጥ ነጥብ ከ10%

1	ፒ.ኤች.ዲ (ሶስተኛ ዲግሪ) የትምህርት ዝግጅት	10
2	ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያለው	9
3	የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያለው	8

12.ለስራ ልምድ አግባብነት የሚሰጥ ነጥብ አፈጻጸም

ማንኛውም ተወዳዳሪ ለስራ መደቡ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የስራ ልምድ አሟልቶ ለውድድሩ ከተመዘገበ በኂላ ለስራ ልምድ የሚሰጠው ነጥብ ከዚህ በታች ባለው መሰረት ይሆናል፡-

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ ለሚወዳደርበት ስራ መደብ የተቀመጠውን ዝቅተኛ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ማሟላት አለበት፤
2. ተወዳዳሪው ለሰራ መደቡ የተቀመጠውን ዝቅተኛ አግባብነት ያለው የስራ ልምድን አሟልቶ ለውድድሩ ከተመዘገበ በኂላ ሰራተኛው ከዝቅተኛው የስራ ልምድ በላይ ላለው አግባብ ያለው የስራ ልምድ በተጨማሪነት ነጥብ ተሰጥቶት በማወዳደሪያ መስፈርትነት ይያዛል፤
3. ለስራ ልምድ አግባብነት የሚሰጠው ነጥብ አፈጻጸም ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ3፡- ለስራ ልምድ አግባብነት የሚሰጠው ነጥብ እንደሚከተለው ይሆናል

ተ.ቁ	የማወዳደሪያ መስፈርት	የሚሰጥ ነጥብ 5%
1	አስር ዓመት ወይም ከአስር አመት በላይ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ፣	5
2	ሰባት ዓመት እና ከአስር ዓመት በታች አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው	4
3	አምስት ዓመት እና ከሰባት ዓመት በታች አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው	3
4	በዋና ር/መምህርነት ወይም ም/ር/መምህርነት እስካሁን በማገልገል ላይ የነበሩ ነገር ግን በመምህርነትና ር/መምህርነት አጠቃላይ አገልግሎታቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ካሉ፣	2

13.ለውጤት ተኮር የስራ አፈፃፀም ምዘና አፈፃፀም

1. የክፍለ ከተማ እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች በከፍተኛ የሀላፊነት ስሜት የውጤት ተኮር የስራ አፈጻጸም አሞላልን ይመራሉ፣ ሚዛናዊነቱንም ያረጋግጣሉ፤
2. ለዚህ ውድድር የሚወሰደው ውጤት ተኮር የስራ አፈፃፀም የሶስት ተከታታይ ሴሚስተር ውጤት ሲሆን ይህም የ2014ዓ.ም የ2ኛ ሴሚስተር እና የ2015 ዓ.ም ሁለቱ ሴሚስተሮች የስራ አፈፃፀም ውጤት አማካይ ይሆናል፤

3. የሶስት ሴሚስተር የውጤት ተኮር የስራ አፈፃፀም ውጤት በወቅቱ ያልተሞላላቸው ተወዳዳሪዎች ለዚህ ውድድር መቅረብ አይችሉም፤
4. የሶስቱ ሴሚስተር ከ100 ፐርሰንት ያላቸው ውጤት ተደምሮ እና ለሶስት ተካፍሎ የሚገኘውን ውጤት ወደ 30 ፐርሰንት በመቀየር የሚወሰድ ይሆናል፡፡

14.የተወዳዳሪዎች የግል ማህደር ጥራት ነጥብ አሰጣጥ ሁኔታ

በከባድ ዲሲፐሊን ቅጣት የተቀጡ ተወዳዳሪዎች ለውድድር አይቀርቡም ሆኖም ቀላል የዲሲፐሊን ቅጣት ያለባቸው ተወዳዳሪዎች ከሚከተሉት ውጤቶች አንዱን በማግኘት ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡

ሰንጠረዥ4፡- የግል ማህደር ጥራት ነጥብ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል

ተ.ቁ.	የተወሰደ የስነ ምግባር እርምጃ	የሚሰጥ ነጥብ ከ 5%
1	ምንም ቅጣት የሌለው፣	5
2	በቃል የተሰጠ ማስጠንቀቂያ በፅሁፍ የተቀመጠ፣	4
3	በፅሁፍ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፣	3
4	እስከ 15 ቀን ደሞዝ የተቀጣ	2

15.የጽሁፍና የቃል ፈተና አሰጣጥ

1. የጽሁፍ ፈተና ከ15 ነጥብ ይሆናል፤
2. የቃል ፈተና ከ5 ነጥብ ይሆናል፤
3. ለአፋን ኦሮሞ ተወዳዳሪዎች ፈተናው በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ይሰጣል፤
4. የፅሁፍ ፈተና ዝግጅትና አሰጣጥን በተመለከተ በትምህርት ቢሮ አማካይነት በጥራትና በጥንቃቄ ተዘጋጅቶ ይሰጣል፤
5. የጽሁፍ ፈተና ውጤቱም ከትምህርት ቢሮ ለክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች ይሰጣል፤
6. የክ/ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎቹም ውጤቱን ለተወዳዳሪዎች በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ያሳውቃሉ፤

7. የቃል ፈተና ለ2ኛ ደረጃ ዋና ርዕሰ-መምህራንና ምክትል ርዕሰ-መምህራን መደብ ላይ ለሚወዳደሩ የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ሃላፊ እና የ2ኛ ደረጃ ክላስተር ሱፐርቪዥን አስተባባሪዎች በመተጋገዝ አዘጋጅተው ይፈትናሉ ውጤቱንም ያሳውቃሉ፤
8. ለቅድመ1ኛ አንደኛ ደረጃና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዋና ርዕሰ-መምህራንና ምክትል ርዕሰ-መምህራን መደብ ላይ ለሚወዳደሩ የወረዳው ትም/ጽ/ቤት ሃላፊ እና የ1ኛ ደረጃ ክላስተር ሱፐርቪዥን አስተባባሪዎች በጋራ አዘጋጅተው ይፈትናሉ ውጤቱንም ያሳውቃሉ፤
9. የፈተናውን ውጤት የጽሁፍና የቃል ተደምሮ 60ከ100 ማለትም 12 ከ 20 ያላገኘ ተወዳዳሪ ከውድድሩ ይሰናበታል፡፡

16.ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ብቃት በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ የሚሰጥ የሚሠጥ ነጥብ

1. ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ብቃት 30 ነጥብ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተወዳዳሪዎች የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ ይሞላል፤
2. ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ብቃት 30 ነጥብ ለቅድመ 1ኛ 1ኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተወዳዳሪዎች የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ 15 ነጥብ እና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ 15 ነጥብ ተከፋፍለው በጋራ ይሰጣሉ፡፡

17.ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ብቃት መመዘኛ መስፈርትና ነጥብ አሰጣጥ

1. ለአመራርነት ክህሎትና ስነምግባር ነጥብ አሰጣጡ ላይ የክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ሃላፊዎች ከግላዊ ፍላጎት በጸዳ መልኩ ስራንና ትክክለኛ ሰራተኛን ለማገናኘት ባለመ መልኩ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 5 እና 6 በተቀመጠው መመዘኛ መስፈርት መሰረት ውጤት የሚሰጡ ይሆናል፤
2. የክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ሃላፊዎች ውጤቱን የሚሰጡት በስራ ወቅት ሲከታተሉበት በነበረው የስራ መመዘኛ መስፈርቶችን፣ የሱፐርቪዥን ግምገማ ውጤቶችንና ሌሎች ተዛማጅ ማስረጃዎችን በማደራጀት ይሆናል፤
3. ውጤቱን ከሰጡ በኋላ በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያላቸው ተወዳዳሪዎችን ማስረጃቸውን በማቅረብ ማሳመን ይጠበቅባቸዋል፡፡
4. **ከዚህ በፊት ዋና ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርእሰ መምህር ያልነበሩ አዲስ ተወዳዳሪ መምህራኖች የአመራር ክህሎትና ስነምግባር መመዘኛ መስፈርት ከ (30%)**

ሰንጠረዥ5፡- ከዚህ በፊት ዋና ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርእሰ መምህር ያልነበሩ

ተ.ቁ	የመመዘኛ መስፈርት	የነጥብ ክብደት ከ30%
1	በስነምግባሩ የተመሰገነ፣ ለተማሪዎች አርአያ የሆነ፣ ታማኝነትና ቅንነትን የተላበሰ ስለመሆን፣	3
2	በሚያስተምርበት ወቅት ተገቢውን ዝግጅት አድርጎ የሚያስተምር እና የክፍለ ጊዜ ብክነት የሌለበት ስለመሆኑ፣	4
3	በመምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም ተማሪዎች ተቀባይነት ያለው ስለመሆን፣	3
4	የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር ማሻሻሉ የተረጋገጠለት ስለመሆኑ፣	5
5	በዲፓርትመንት ክበባትና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የነበረው ውጤታማ ተሳትፎ፣	3
6	ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲሰፍን ለማድረግ የነበረው ወሳኝ ሚና፣	3
7	የትምህርት ሴኩላሪዝምን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የነበረው ተነሳሽነትና ጥረት፣	3
8	በአጠቃላይ አፈፃፀሙ ትምህርት ቤቱን ሞዴል ለማድረግ የነበረው ተሳትፎና ሚና፣ (ለምሳሌ በከተማ ግብርና እና የትምህርት ቤት አካባቢ ጥበቃን በማከናወን የነበረው ጥረት እና ሌሎች---፣)	3
9	የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በብቃት ለስራ መጠቀም፣	3
	ጠቅላላ ድምር	30

5. **ከዚህ በፊት ዋና ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርእሰ መምህር የነበሩ ተወዳዳሪዎች የአመራር ክህሎት መለኪያ መስፈርት ነጥብ ዝርዝር አፈጻጸም (30%) መመዘኛ መስፈርት፣**

ሰንጠረዥ6፡- ከዚህ በፊት ዋና ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርእሰ መምህር የነበሩ

ተ.ቁ.	የመመዘኛ መስፈርት	የነጥብ ክብደት ከ(30%)
1	በኢንስፔክሽን ፍረጃ ውጤት የትምህርት ቤቱን ደረጃ ከነበረበት ያሻሻለ፣ ወይም ባለበት ደረጃ ሆኖ ከነበረው ውጤት ያደገ ስለማስመዝገብ፣	5
2	የትምህርት ቤቱን ሃብትና ንብረት ባግባቡ ስለመጠቀምና ብክነትን ስለመከላከል፣	3
3	በትምህርት ቤቱ ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲሰፍን የነበረው የአመራር ሚና፣	4
4	በትምህርት ቤቱ የትምህርት ሴኩላሪዝምን ጠብቆና አክብሮ ስለመስራት እና ሌሎች እንዲጠብቁና እንዲያከብሩ ስለማድረግ፣	4
5	የ8ኛ/12ኛ ክፍል በከተማ እና ሃገር አቀፍ ፈተና ውጤት ከ50 ፐርሰንት እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በየአመቱ ባደረገው መሻሻል መጠን፣ (አመራር በሰጠባቸው አመታት አማካይ የሚወሰድ)	10
6	**በመልካም አስተዳደር ችግርና በሌብነትና ብልሹ አሰራር የማይታወቅ፣**	2
7	**የስራ ስነምግባርን ስለማክበርና ስለማስከበር፣ ከስራ ኃላፊዎችና ከስራ ባልደረቦች ጋር ያለ መልካም ግንኙነት፣**	2
	ጠቅላላ ውጤት	30

18. **ስለ ተጨማሪ ድጋፍ**

1. ሴት ተወዳዳሪዎች በሚወዳደሩበት ጊዜ በህግ በተፈቀደላቸው የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነት መሠረት አጠቃላይ ነጥብ ውጤት ከታወቀ በኋላ እስከ **ሶስት ነጥብ** ውጤት ልዩነት ሲኖር ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይደለደላሉ፤
2. አካል ጉዳተኞች በሚወዳደሩበት ጊዜ ባገኙት የነጥብ ድምር ላይ ለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አስመልክቶ በወጣው የአፈጻጸም መመሪያ **እስከ አራት ነጥብ ድረስ** ልዩነት ካላቸው ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይደለደላሉ፤
3. አንድ ተወዳዳሪ ከአንድ በላይ አዎንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ ከሆነ /ለምሳሌ ሴት እና የአካል ጉዳተኛ በመሆን/ የሚያሰጠው የአዎንታዊ ድጋፍ **5 ነጥብ** ይሆናል፤
4. ተመሳሳይ ወይም የተለያየ መጠን ያለው አዎንታዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ዕጩዎች በውድድር እኩል ውጤት ካመጡ ቅድሚያ **በሥራ አፈጻጸም**፣ ከዚያ **በትምህርት ደረጃ** እና **የሥራ ልምዳቸው** እንዲበላለጡ ይደረጋል፤
5. ከላይ በተራ ቁጥር 4 በተቀመጠው መሠረት ተወዳዳሪዎቹን መለየት ካልተቻለ ተወዳዳሪው በሚገኝበት ክፍለከተማ ወይም ወረዳ ኃላፊ በሚሞላና ከ10 ነጥብ በሚያዝ የሥራ አፈፃፀም ምዘና እንዲለዩ ይደረጋል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 የተቀመጠው 10 ነጥብ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

   ሀ) ለዕቅድ ክንውንና ሥራዎችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መፈፀም 5

   ለ) ተገልጋዮችን በተገቢው መንገድ ማስተናገድ 3

   ሐ) በሥራ ላይ ያለው ሥነ-ምግባር..2 ፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ስለ ድልድል ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ተግባርና ሃላፊነት</u>

<u>19.የትምህርት ቢሮ የድልድል አስፈፃሚ ኮሚቴ አወቃቀር</u>

1. በትምህርት ቢሮ ደረጃ አቢይ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ ይዋቀራል፤
2. በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋመው አቢይ ኮሚቴ የትምህርት ቢሮ ሃላፊ፣ የትምህርት ቢሮው ም/ሃላፊዎች፣ የትምህርት ቢሮ ሃላፊ አማካሪዎች፣ የትምህርት ቢሮው ጽ/ቤት ሃላፊ፣ ቴክኒካል አማካሪ፣ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎችን እና የከተማ መምህራን ማህበርን ያካተተ ይሆናል፤

3. በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋመው የድልድል አስፈፃሚ ቴክኒክ ኮሚቴ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡

20. በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋም የድልድል አስፈፃሚ አቢይ ኮሚቴ ጥንቅርና ብዛት

1. የትምህርት ቢሮ ሃላፊ--(1) ሰብሳቢ፤
2. ም/ቢሮ ሃላፊዎች--(3) አባል፤
3. አማካሪዎች ---(2) አባል፤
4. የጽ/ቤት ሃላፊ---(1) አባል፤
5. ቴክኒካል አማካሪ --(1) ፀሃፊ፤
6. የክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች----------------------(11) አባል፤
7. የከተማ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ----------------------------(1) አባል፡፡

21. በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋም የድልድል አስፈፃሚ አቢይ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. የድልድሉን ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
2. የቴክኒክ ኮሚቴውን አሰራርና ሂደት ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤
3. በክፍለ ከተማ እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የተሰራውን የድልድል ስራ እንደ ትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ስብጥሩንና ፍትሃዊነቱን በመገምገም ያፀድቃል፤
4. የአሰራር ሂደቱን ያያል፣ ይገመግማል፣ ለችግሮች የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ተጠያቂነትን ያሰፍናል፡፡

22. በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋመው የድልድል አስፈፃሚ ቴክኒክ ኮሚቴ ጥንቅርና ብዙት

1. በትምህርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም………………………………… (1) ሰብሳቢ፤
2. የአፋን ኦሮሞ ስርአተ ትምህርት ማበልጸግና ትግበራ ዳይሬክተር…………. (1) አባል፤
3. የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር………. (1) ጸሀፊ፤
4. የስርአተ ትምህርት ማበልጸግና ትግበራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር………… (1) አባል፤
5. የፈተናና ምዘና ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር……………. (1) አባል፤
6. የትምህርት ቤት መሻሻልና ግብአት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር……………… (1) አባል፤
7. የከተማው መምህራን ማህበር ስርአተ ፆታ ሃላፊ/ተወካይ …………………. (1) አባል፡፡

23.በትምህርት ቢሮ ደረጃ የሚቋቋመው የድልድል አስፈፃሚ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. በወረዳ እና ክፍለ ከተማ ደረጃ ስለሚካሄደው ድልድል የድርጊት መርሃ-ግብር ያዘጋጃል፤
2. ስለ መመሪያው እና ስለመዋቅር አደረጃጀት ጥናቱ ኦሬንቴሽን ይሰጣል፤
3. በየደረጃው የሚደራጁ ኮሚቴዎችን አሰራር ይደግፋል፤
4. ለዋና ር/መምህራን፣ ም/ር/መምህራን የጽሁፍ ፈተና ያዘጋጃል፣ ይፈትናል፡ ያርማል ያስፈፅማል፤
5. ስለአፈፃፀሙ ለአቢይ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፤
6. ለሰራቸው ስራዎች ሙሉ ተጠያቂነት ይወስዳል፤
7. አጠቃላይ የውድድር ሂደቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ያስተካክላል ይሰርዛል፡፡

24.የድልድል ኮሚቴ አደረጃጀት

1. በክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድልድል ኮሚቴ ይቋቋማል፤
2. በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የቅድመ አንደኛ 1ኛ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድልድል ኮሚቴ ይቋቋማል፤
3. በክፍለ ከተማ እና በወረዳ የሚቋቋመው ኮሚቴ አምስት **አምስት አባላትና አንድ ድምጽ የሌለው ጸሐፊ ያለው** ይሆናል፤
4. ከአባላት መካከል አንደኛዋ ሴት መሆን ይኖርበታል፡፡

25.በክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚደራጅ የድልድል ኮሚቴ ጥንቅርና ብዛት

1. በትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰየም... (1) ሰብሳቢ፤
2. የክፍለ ከተማ የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ቡድን መሪ/ተወካይ.... (1) አባል፤
3. የአፋን ኦሮሞ ስ/ትም/ቡድን መሪ --- (1) አባል፤
4. የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽ/ቤት የሚገኝበት ፑል የሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን መሪ/ተወካይ ....(1) አባል፤

5. የክፍለ ከተማ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ ተወካይ.............................. (1) ጸሀፊ ይሆናሉ፡፡

26.በክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚደራጅ የድልድል ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. ለሚያከናውናቸው ተግባራት የድርጊት መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤
2. በመዋቅር ጥናት እና በስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ፀድቆ የመጣውን የሥራ መደቦች ዝርዝር ይረከባል፤
3. የሥራ መደብና ደረጃዎች ለተወዳዳሪዎች ግልጽ በሆነ ቦታ በመለጠፍ ተወዳዳሪዎችን በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ምዝገባ ያካሂዳል፤
4. በመመሪያው ላይ በተገለፀው መሠረት ተወዳዳሪዎችን ያወዳድራል፤
5. ከምዝገባ ስራው ጀምሮ እስከ ማጠናቀቂያ ስራዎች ድረስ ሂደቱን በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤
6. የውድድር ሥራውን ሚስጢር ይጠብቃል፤
7. የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ይሰጥበታል፤
8. የድልድል ኮሚቴውን ውሳኔው ለቢሮው አቢይ ኮሚቴ አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደረጋል፤
9. ድልድሉ እንደገና እንዲታይ ከበላይ ሃላፊ ሲታዘዝ መመሪያውን መሰረት በማድረግ እንደገና ያያል፤ ማየት ካልቻለ ከነ ምክንያቱ ያሳውቃል፤
10. አንድ የድልድል ኮሚቴ አባል የራሱ ውድድር ሲታይ ከኮሚቴው ስብሰባ መውጣት ይኖርበታል፤
11. ኮሚቴው ለሰራቸው የድልድል ስራዎች ተጠያቂነት አለበት፡፡

27.በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚደራጅ የውድድር ኮሚቴ ጥንቅርና ብዛት

1. በትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰየም....................................... (1) ሰብሳቢ፤
2. የወረዳው የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ባለሙያ/ተወካይ.......... (1) አባል፤
3. የአፋን ኦሮሞ ስ/ትም/ ባለሙያ --(1) አባል፤
4. የወረዳው የሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን መሪ/ተወካይ..................................(1) አባል፤
5. በወረዳው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከአንዱ የመሰረታዊ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ ተወካይ... (1) ጸሀፊ ይሆናሉ፡፡

28.በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚደራጅ የድልድል ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. ለሚያከናውናቸው ተግባራት የድርጊት መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤
2. በመዋቅር ጥናት እና በስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ፀድቆ የመጣውን የሥራ መደቦች ዝርዝር ይረከባል፤
3. የሥራ መደብና ደረጃዎች ለተወዳዳሪዎች ግልጽ በሆነ ቦታ በመለጠፍ ተወዳዳሪዎችን በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ምዝገባ ያካሂዳል፤
4. በመመሪያው ላይ በተገለፀው መሠረት ተወዳዳሪዎችን ያወዳድራል፤
5. ከምዝገባ ስራው ጀምሮ እስከ ማጠናቀቂያ ስራዎች ድረስ ሂደቱን በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤
6. የድልድል ሥራውን ሚስጢር ይጠብቃል፤
7. የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ይሰጥበታል፤
8. የድልድል ኮሚቴውን ውሳኔው ለቢሮው አቢይ ኮሚቴ አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደረጋል፤
9. ድልድሉ እንደገና እንዲታይ ከበላይ ሃላፊ ሲታዘዝ መመሪያውን መሰረት በማድረግ እንደገና ያያል፤ ማየት ካልቻለ ከነ ምክንያቱ ያሳውቃል፤
10. አንድ የድልድል ኮሚቴ አባል የራሱ ውድድር ሲታይ ከኮሚቴው ስብሰባ መውጣት ይኖርበታል፤
11. ኮሚቴው ለሰራቸው የድልድል ስራዎች ተጠያቂነት አለበት፡፡

29.የድልድል ስራን በሚመለከት

ድልድል እንደተጠናቀቀ ለዋና ር/መምህርነትና ም/ር/መምህርነት መደብ ያለፉ ተወዳዳሪዎች የሚደለደሉበትን ትምህርት ቤት በሚመለከት፡-

1. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ስብጥር ሰርተው የውሳኔ ሃሳብ ለቢሮው አቢይ ኮሚቴ አቅርበው በማፀደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፤
2. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች ከክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች ጋር በጋራ በመሆን የቅድመ1ኛ፣ 1ኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ስብጥር ሰርተው የውሳኔ ሃሳብ ለክፍለ ከተማው ያቀርባሉ፤
3. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች የወረዳውን የቅድመ1ኛ፣ 1ኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድልድል ስራም በጋራ ሰርተው ውጤቱን ለቢሮው አቢይ ኮሚቴ አቅርበው በማፀደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

ክፍል አምስት

ስለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

30. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

1. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በክፍለከተማ እና በወረዳ ደረጃ ይደራጃል፤
2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ 3 አባላት ይኖሩታል፤
3. የድልድል ኮሚቴ አባል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል መሆን አይችልም፡፡

31.የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚዋቀር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጥንቅርና ብዛት፣

1. በክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ የሚሰየም............................... ሰብሳቢ፤
2. የክፍለ ከተማው መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ተወካይ .... አባል፤
3. የአመራር ልማት ባለሙያ-----------------ፀሃፊ ይሆናሉ፡፡

32.የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ የሚዋቀር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጥንቅርና ብዛት፣

1. በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ የሚሰየም.......... ሰብሳቢ፤
2. በወረዳው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ መምህራን ማህበር አንዱን ሰብሳቢ/ተወካይ -----------አባል፤
3. የወረዳ መምህራን ልማት ባለሙያ/ተወካይ---------------------ፀሀፊ ይሆናሉ፡፡

33.የክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፤

1. ከአድሎአዊ አሰራር ነጻ ሆኖ የተሰጠውን ሀላፊነት ይወጣል፤
2. ውድድር ጸድቆ ይፋ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ከውድድር ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ የቅሬታ

   ማመልከቻዎችን ይረከባል፤
3. በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅሬታዎችን አጣርቶ የውሣኔ ሀሣብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤
4. የቅሬታ ማመልከቻዎችን፣ በማጣራት ሥራ የተገኙ ማስረጃዎችን እና ቃለ-ጉባኤዎችን

   አደራጅቶ ይይዛል፤
5. የአጠቃላይ ክንውን ሪፖርት ለበላይ ሀላፊ ያቀርባል፡፡

34.የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. ድልድሉን አስመልክቶ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ተወዳዳሪ ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፤

2. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የተወዳዳሪዎቹን በጽሁፍ የቀረበ ቅሬታ አጣርቶ ለበላይ ሀላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
3. በአመራር ብቃትና ስነምግባር መመዘኛ መስፈርት የተሰጡ የ30 ነጥብ ቅሬታ ለክፍለ ከተማ እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች ቀርቦ የመጨረሻ ምላሽ ይሰጡበታል እንጂ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታነት አይቀርብም፡፡

35.ቅሬታ የሚቀርብበት ጊዜ፤

1. በድልድሉ ቅሬታ አለኝ የሚል ተወዳዳሪ ውድድሩ ፀድቆ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት **አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ** ቅሬታውን በጽሁፍ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታውን ማቅረብ ያልቻለው በአሳማኝ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ **ለሶስት ተከታታይ ተጨማሪ የሥራ ቀናት** ሊራዘም ይችላል፤
3. በስራ አፈጻጸም ውጤት ቅሬታ ያለው ሰራተኛ የውድድር ስራው ከመጀመሩ በፊት በሶስት የስራ ቀናት ብቻ ለበላይ ሀላፊ ያቀርባል፡፡

36.የቅሬታ ውሣኔ አሰጣጥን በተመለከተ

1. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታው በጽሁፍ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ **በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ** የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ የበላይ ሃላፊ ማቅረብ አለበት፤
2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመው በስተቀር የቀረበለትን ቅሬታ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
3. የበላይ ኃላፊው ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ በቀረበለት እስከ አምስት ስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

37.ይግባኝን በተመለከተ

1. በክ/ከተማና በወረዳ፣ በሚካሄደው ድልድለ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ቅድሚያ ለክፍለ ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት የቅሬታና አቤቱታ ቡድን የሚያቀርብ ይሆናል፤
2. በክፍለ ከተማ ቅሬታና አቤቱታ ቡድን በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ የቅሬታና አቤቱታ ዳይሬክቶሬት የሚያቀርብ ይሆናል፤
3. የቢሮ ቅሬታና አቤቱታ ዳይሬክቶሬት በሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

38.ሪፖርት ስለማቅረብ

ድለድል እንደተጠናቀቀ አጠቃላይ ሪፖርት እንደሚከተለው ይቀርባል፣

1. የቢሮው ቴክኒክ ኮሚቴ በወረዳዎችና ክ/ከተሞች የተሰራው ስራ ሪፖርት በየደረጃው ባለ አመራር ታይቶና ጸድቆ ለቢሮው እንዲላክ ይደረጋል፤
2. የድልድል ስራው በክፍለ ከተማና በወረዳ በአመራር ደረጃ ተገምግሞ እና በሚመለከታቸው ሀላፊዎች ጸድቆ በክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት በኩል ተደራጅቶ ለአቢይ ኮሚቴ ይላካል፡፡

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

39.ስለተጠያቂነት

1. የበላይ ሀላፊው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖረው በተቀመጠለት ጊዜ ገደብ ውሳኔ ካልሰጠ እና በሚጠበቀው ደረጃ ሂደቱን ካልመራው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤
2. የውድድር ኮሚቴው በተቀመጠው በህጉ መሰረት በማከናወን የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ካልቻሉ በአዋጁ አንቀፅ 70 በከባድ ዲሲፕሊን ቅጣት ከተዘረዘሩት መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤
3. ይህን መመሪያ ሆን ብሎ የተላለፈ በአዋጁ አንቀጽ 94/3 በተገለጸው መሠረት አላግባብ ውጤት ከሰጠ፣ ውድድር ካካሄደ፣ ወይም ድልድል ከሰጠ "በከባድ ቸልተኝነት" ህግ ተጠያቂ ይሆናል፤
4. የትምህርት ቢሮ የድልድል አፈጻጸም ሂደቱን ይገመግማል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊው ሆኖ ሲያገኘው የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ይሰርዛል፤
5. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለቢሮው አቢይ ኮሚቴ እየቀረበ ውሣኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

40.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ጉዳዮች፤

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም የቢሮው መመሪያና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

41.ስለተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ በፊት ስራ ላይ የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና ምክትል ርዕሰ መምህራን የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 129/2014 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

42.የመመሪያው ተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመሪያ የሚያገለግለው በትምህርት ቤቶች መዋቅር ክለሳ ጥናት ለተፈጠሩ የዋና ር/መምህራንና ም/ር/መምህራን መደቦች ድልድል ለመስጠት **ለአንድ ጊዜ ብቻ** የሚያገልግል ይሆናል፡፡

43.ልዩ ልዩ ቅጾች

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚያግዙ ልዩ ልዩ ቅጾች የዚህ መመሪያ አካል ሆነው ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

44.ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በፍትህ ሚኒስቴር እና በቢሮ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም 2016 ዓ.ም

ሂክማ ከይረዲን

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰውሃበት ልማት ቢሮ ኃላፊ